# በቅንጅት አለማቀፍ የፖለቲካ አመራር አባላት መካከል የተፈጠረውን ችግር በመግባባት ለመፍታት የተፈረመ የመግባቢያ ሰነድ

የፓርቲያችን የቅንጅት ለአንድነትና ለዳሞክራሲ መሪዎች በኢህአዴግ መንግስት በተወሰደ የማናለብኝነትና የህግ የበላይነትን የጣሰ እርምጃ ምክንያት በሃሰት ተወንጅለው በእስር በመማቀቅ ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል:: የፓርቲው መሪዎች፣ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የፓርቲውን ድርጅታዊና ፖለቲካዊ ስራዎች እንዲያስተባብር በማሰብ፣ አስራ ሁለት ሰዎችን ያካተተ «ቅንጅት አለማቀፍ የፖለቲካ አመራር ኮሚቴ» ቀደም ሲል ሰይመዋል::

መሪዎቹ ይህንን አካል ሲሰይሙ፣ ቅንጅት ከህዝብ የተጣለበትን ከባድ አደራና ሃላፊነት ለመወጣት እንዲችልና ትግሉም ለድል በሚያበቃ መልኩ እንዲካሄድ የመምራት ሃላፊነታቸውን በከፊል በውክልና በማስተላለፍ ነበር:: ይህ ከፍተኛ ድርጅታዊና ሃገራዊ ሃላፊነት የተጣለበት አካል፣ በአባላቱ መካከል በተፈጠረ ያለመግባባት ምክንያት የተጣለበትን ሃላፊነት በአጥጋቢ ሁኔታ ለመወጣት አልቻለም:: በመሆኑም በጠቅላላው የፓርቲው እንቅስቃሴ ጠሚጠበውን ያህል ውጤት አላሳየም::

እረዘም ላለ ጊዜ ይህንን ችግር ለማቃለልና የተፈጠሩ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል:: በተለይ ላለፉት አራት ወራት፣ ከኢትዮጵያ በመሪዎቻችን ይሁኝታና አሳሳቢነት ሁለት ከፍተኛ የቅንጅት አመራር አባላት አሜሪካን አገር ድረስ በመምጣት፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የአመራር አባላት፣ የተለያዩ የድጋፍ ድርጅቶችን፣ የቅንጅት አባላትና ደጋፊ ግለሰቦችን አነጋግረዋል:: እርቅንና ሰላምን ለማምጣት የተለያየና ከፍተኛ ጥረትን አካሂደዋል:: ይህውም ሆኖ ግን ሰላምና እርቅ ሊወርድ አልቻለም፣ ችግሩም ሳይወገድ ቆይቶአል::

የቅንጅት መሪዎች የተፈጠረውን ችግር በተመለከተ የተሰማቸውን መሪር ቅሬታ ገልጸው፣ ተማጽኖ የተቀላቀለበት መመሪያና የፖለቲካ ውሳኔ አክለው፣ በሁለቱም ወገን ያሉት በአስራምስት ቀን የጊዜ ገደብ ውስጥ ችግሩን በእርቅ ለመፍታት እንዲስማሙ ትእዛዝ አስተላልፈዋል:: በላኩት መልእክትም ላይ በግልጽ «እርቁ በጊዜያዊ ጫናን ለማስወገድ የሚደረግ ሳይሆን ልባዊ፣ ዘላቂ፣ በተግባር የማታይና በታሪካችን በምሳሌነት የሚጠቀስ መሆን አለበት» ብለው ገልጸዋል::

ይህንን መሰረት በማድረግ ስማችን ከግርጌ የተጠቀሰው አስራ ሁለት የቅንጅት አለማቀፍ የፖለቲካ አመራር አባላት:-

1. ከዚህ በላይ በአጠቃላይ መልኩ በቀረበው መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄደ ያለው ትግል ያላግባብ መንተቱን በማመን፤
2. በመካከላችን የተፈጠረው ችግር በኢትዮጵያ ህዝብና በተለይም በፓርቲያችን ደጋፊዎች ላይ ያስከተለውን ቅሬታ በመገንዘብ፤
3. በእስር ቤት በመማቀቅ ላይ ያሉ መሪዎቻችን በኛ መካከል በተከሰተው ሁኔታ ቅሬታ የተሰማቸው መሆኑን በመረዳት፤
4. ጉዳዩን በሰላምና በመግባባት በመጨረስ የችግሩን ምንጭ ማድረቅ ለትግሉ ወሳኝነት ያለው መሆኑን በማመን፤

   ሀ. ከቅንጅት ፓርቲ መሪዎች ውክልና ያለውና የቅንጅትን ድርጅታዊና የፖለቲካ ስራ የሚመራው እኛ በአባልነት የምንገኝበት ቅንጅት ያለምአቀፍ አመራር ብቻ መሆኑን ሁላችንም ተቀብለናል::

ሰ. እስካሁን ለተፈጠረው ችግር ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በቅንጅት መርህና በዲሞክራሲያዊ መንገድ ለማስተካከል ወስነናል።
ሐ. በተሰጠን የውክልና ማእቀፍ ውስጥ ጠንካራ ድርጅታዊ አመራር በጋራ ለመስጠትና የባከነውን የትግል ጊዜ ለማካካስ የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን።

ይህን መግባቢያ ሰነድ ወደንና ፈቅደን በቅን ልቦና አጽድቀናል። ይህም ለቅንጅት መሪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ይፋ እንዲደረግ ተስማምተናል።

የስምምነቱ ተሳታፊዎች

1. ዶ/ር ሞገስ ገብረማሪያም
2. አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ
3. አቶ ብርሃነ መዋ
4. አቶ ዳንኤል አሰፋ
5. ዶ/ር ገብርዬ ወልደሩፋኤል
6. አቶ ማሞ ይሁኔ
7. አቶ ጌታቸው ዋና
8. አቶ ዳዊት ከበደ

1. ሻለቃ ዮሴፍ ያዘው
2. ዶ/ር ስዩም ሰለሞን
3. ዶ/ር አልማዝ ዘውዴ
4. አቶ ሰለሞን በቀለ

ታዛቢዎች

1. ዶ/ር በዛብህ ደምሴ
2. ሻለቃ አድማሱ መላኩ
3. ፕሮፌሰር ኧስማየሁ

4. ዶ/ር ሰለሞን ኧስለው
5.
6.

ተወካዮች

ዶ/ር ሞገስ ገብረማሪያም (signed)

ዶ/ር በዛብህ ደምሴ (signed)

ሻለቃ ዮሴፍ ያዘው (signed)

ይህ ሰነድ ሰኔ ፱ ቀን 1999 ዓ.ም በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ ተፈረመ